# PANORAMA # XVLIII

## የትዝብት አድማስ

መስከረም 16 ቀን 2001 ዓም

### ፀንቶ ታጋዩን ማጠናከር ሀገር አዳኝ ነው

በአሁን ጊዜ በኢትዮጵያ የፖሊቲካ ትግል መድረክ ያለውን የኃይሎች አሰላለፍ በሚገባ ማጤንና መፈረጅ እጅግ በጣም አስፈላጊና አንገብጋጅ ጉዳይ መሆኑን ያልተረዱ ክፍሎች፥ አሁንም የሽረሪት ድር ያደራባቸው ይመስላል:: አውቀውትምይሁን ሳያውቁት፥አሁንም እንደ ትላንቱ፥ብዙ የሀገራችን ነገሮች አልተከሰቱላቸውም:: የሀቀኛውን ታጋይ ኃይል መሸርሸር፥ የቱን ያኅል የወያኔን ዕድሜ እንደሚያስረዝምና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰቆቃ እንሚያበራክተው አልተረዱትም:: የኢትዮጵያን ወደጥፋት ጎዳና የመሄዱን ፍጥነትም ምንኛ እንደሚያጣድፉትም ጭራሽ አለተገነዘቡትም፥ ወይም ሆን ብለው በአቋም ደረጃ አምነውበት፥ በወያኔ አገዛዝ መሰንበት ወስነዋል ማለት ነው:: ተሳስተውም ይሁን ገብቷቸው፥ ይህ የሚያደርጉት ድርጊትና የያዙት አቅጣጫ፥ በታሪክና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው ግን ማወቅ አለባቸው:: ፊትን ቢጠሉ አፍንጫን አይቆርጡ የተባለውን የፈረንጆች ተረት ያስታውስናል:: “አይተነው ጊዜ ወደ አደላበት” የሚባለው የፖሊቲካ ብልጣ ብልጥነትና የአበላባዮች ጨዋታ፥ በአሁኑ የኢትዮጵያ የፖለቲካ አድማስ ቦታ ሊኖረው እንደማይችል መገንዘብ ብልኅነት ነበር:: በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ንቃተ-ኅሊናን እንደ አልባሌ እያዩ በትዕቢት መወጠር ትርፉ ትዝብት እንጅ የሚያመጣው ፋይዳ የለውም::

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ አምባ ሊኖር የሚችለው ሁለት ተፃራሪ ጎራ ብቻ ነው:: ወያኔ በአንድ በኩል፥ ወያኔን ተፃርረው የቆሙ ሀገር ወዳድ ተቃዋሚ ኃይሎች በሌላ በኩል:: ይህ የፖሊቲካ ዕውነታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ፀሀይ ግልፅ እንጅ የተሰወረ አይደለም:: በማንኛውም ኅብረተሰብ፥ የመሃል ሰፋሪነት ድርጊትና ባህርይ መኖር ባያስገርምም፥ በቀውጢ ቀን፥ሀገር የሰው ያለህ በምትልበት ወቅት መሃል ሰፋሪ መሆን ከታሪክ ጀምሮ፥የሚያኮራ ሳይሆን፥ የሚጎዳና የሚያስተዛዝብ ነው:: ተቃዋሚ ነኝ ብሎ በወያኔ ጀርባ መሰለፍና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፎ መቆም የጨለማና የብርሃን ያህል ልዩነት አለው:: ዛሬ በሚታየው የኢትዮጵያ የኃይሎች አሰላለፍና የፖለቲካ ሂሳብ ስሌት መሠረት፥ አይኑን አፍጥጦ የመጣው ሁለት ጎራ ብቻ መኖሩን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል:: ለጊዜውም ቢሆን፥ የነመለስ ዜናዊን ጉጅሌ/ ቡድን በፖሊቲካው የዳማ ጨዋታ ሳናስገባ ማለታችን ነው:: በዚህ አፈረጃጀት፥የፖሊቲካው ሂሳብ ቢደመር፥ ቢቀነስ፥ ቢበዛና ቢካፈል፤ የሚያስገኘው ዉጤትያው ዞሮ ዞሮ አንድ ብቻ ነው:: ሁሉም ዜሮ ዜሮ መሆን ነው:: ይህን ለመረዳትደግሞ ሌላ የተራቀቀ የሂሳብ ዕውቀትና ሥራን

አይጠይቅም:: ወያኔን ተፃርረን ቆመናል የሚሉ ጥቂት ድርጅቶች ብሎም በተቃዋሚ ስም የወያኔን ዕድሜ ለማራዘም የተለያዩ ኃሳዊ ቀለማት ተቀብተው እንደ ሽማኔ መወርወሪያ የሚባዝኑ ክፍሎች ናቸው:: ይህ የፖሊቲካ የገበጣ ጨዋታ ደግሞ ከሁሉም የበለጠ እየጠቀመው ያለው፥ ለጊዜውም ቢሆን፥ መለስንና ግብረ-አበሮቹን ብቻ ሆኗል:: በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል መድረክ ይህ ሁኔታ ግልፅ ሆኖ የቀረበ በመሆኑ፥ማን ማንን ሊያታልል የሚችልበት አንዳችም ታምር አይኖርም:: የፖለቲካ ጥብቆንና የዕበላ ባይነትን ማተብ እየለዋወጡ በሦስት ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች ውስጥ መኖር ተችሎ ይሆናል፥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ የፖለቲካ ዕውነታ ግን፥ እንደ ትላንቱ በሁለት ቢላዎች ለመብላት መሞከር የሚቻል የሚሆን እንዳልሆነ የብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ስምምነት ከሆነ ውሎ አድሯል:: ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ይቀርባሉ:: አንደኛው፥ የኢትዮጵያ የፖሊቲካ መልከዓ-ምድር ቀደም ብሎ ከነበረው በብዙ መልኩ የተለወጠ መሆኑ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ብስለትና ተራማጅ አስተሳሰብ ምጥቀት አንድ ከፍተኛ ደረጃ መድረሱ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህልና ሥነልቦና ከሚጠላቸውና ከሚንቃቸው ባኅርያት አንዱ፥ በሁለት ቢላዎች መብላትና እንደ እስስት መለዋወጥን ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በዕምነቱ ቆሞ የሚታገለውን ኃይል፣ አመኔታንና ክብር ይሰጠዋል::

> "በእምነቴ ልገዛ፥ በማተቤ ልዳኝ
> በታሪክ ፈራጅነት፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕማኝ፥
> ሌላም ዳኛ ሌላም ጠያቂ የለኝ :: "

የሚባለውም ለዚሁ ነው:: አስመሳይ ቀለማትን እየተለቀለቁ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን የማይበገር አቋም፥ትኩረትና አቅጣጫ ለማሳት መከጀል፥ ወያኔን ከመጥቀም በስተቀር፥ የሚያስገኘው አንዳችም ፋይዳ አይኖረውም:: ይህ ደግሞ የሚያስከትለው፥ በትውልድ መጠላትንና መናቅን፥ በታሪክ ፊት መፈረድንና መዋረድን ብቻ ነው:: ይዋልም-ይደር እንጅ፥ ዕውነቱ ነገ እንደሚከሰት ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል! የሃይማኖት መጽሀፍት ሳይቀሩ "ዕውነት ነፃ ታወጣለች" ያሉትም ያለምክንያት አልነበረም::

አይበገሬ ድርጅቶች ታዲያ፥ ጉዟቸውን ገምግመው፥፥ ስህተታቸውንና ድክመታቸውን ለይተው በማውጣት አስተካክለው፥ የትግል ቃል-ኪዳናቸውን በአዲስ መልክ አጠናክረው የወደፊቱንም የትግል አቅጣጫቸውን ቀይሰው መውጣቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ እንደገና የሚያለመለመውና የወያኔንም ጎራ ቅስም እንደሚሰበር፥ የሚካድ አይደለም:: " ቂጣ ከሆነ ይሚሸሻል፥ ፅንስም ከሆነ ይገፋል" እንደሚባለውም፥ በትግሉ መርዘምና ከባድ መስዋዕትም የሚጠይቅ በመሆኑ፥ ቅስማቸውን የሰበረባቸው መሃል ሰፋሪዎች፥በአሁኑ ወቅት ዕውነተኛ ገፅታቸውን በሚገባ በማሳየታቸው፥ ከሁሉም በላይ ያስደሰተው ቢኖር፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ነው:: ምክንያቱም፥ የቂጣውን መሚሸሽና ፥ የፅንሱንም እየገፋ መሄድ በመረዳቱ ነው:: በአሁኑ ወቅት፥ ማን ዕውነተኛ

ታጋይ ማንስ ተነፋራ ታጋይ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ስለአወቀ፥ ትልቅ የመንፈስ ርካታን አግኝቶ፥ በወያኔ ላይ የማያወላውል አቋም በመያዝ አምርረው የሚታገሉትን አይበገሬ ድርጅቶች፥ በሁለንተናዊ መልኩ ለመርዳት ተነሳስቷል። ይህንንም ውሳኔ ለመውሰድ የበቃው፥ለኢትዮጵያ ትንሳዔ ማን እንደቆመና ኃሳዊ- መሲሄዎቹ ደግሞ ማን እንደሆኑ በሚገባ ለማወቅ ዕድል በማግኘቱ ነው። አሁን ሁሉም ነገር ነጥሮ ወጥቷል። ያለው ጎዳናም ሁለት ብቻ ሆኗል። አንደኛው ወያኔን ተፃርሮ የቆመውና ለኢትዮጵያ ትንሳዔ አምርሮ የሚታገለው ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ ከነመለስ ጋር ተዘንቆ የሥልጣን ምፅዋዕት ለማግኘት የተኮለኮለውና በቆራጥ ታጋዮች ላይ አዲስ ዘመቻ የከፈተው ነው። ለዚህም ፍርዱና ውሳኔው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማይታበል ይሆናል። ጊዜና ትውልድም የራሳቸው ብያኔ ይኖራቸዋል። ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ገበታ ውሃ መዋለልና ወለም ዘለም እያሉ ሕዝብን የማታለል የቁማር ጨዋታ አክትሟል። በሁለት ባላዎች ተመርኩዝ፥ አንዱ ሲሰበር በሌላው ተንጠልጠል የሚባለው ማታለል አብቅቷል። በተቃዋሚ ስም ሁለት በርኖስ መልበስ ከቶ አያዋጣም። ወይ ተቃዋሚ ሆኖ መለስንና አጥፊ የዘር ፖለቲካውን አምርሮ መታገልና ይህን ዘረኛ ሥርዓት ማስወገድ፥ ካልሆነ ደግሞ፥ በመለስ ጎራ መሰለፍና በግልፅ ደግፎ የሥርዓቱ አባሪ ተባባሪ መሆን ብቻ ነው። ሁለት እግሮች ስለአሉ ብቻ ሁለት ዛፎች ላይ በአንድ ጊዜ መውጣት አይቻልም። በምትኃት ካልሆነ በቀር! ምትኃት ደግሞ በፖሊቲካ ትግል የሚሰራ አይሆንም። ልስራ ቢልም ቆራጥ ታጋዮችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብረው ያከስሙታል።

የኢትዮጵያ ሀገራችን ችግሯ ብዙ፥ ጥልቅና ውስብስብ መሆኑ ተደጋግሞ ተደጋግሞ የተነገረ፥ የተፃፈና ያንገፈገፈም በመሆኑ፥ ያንኑ መድግም እኛም ራሳችን ሰልችቶናል። የኢትዮጵያ ፈርጀ-ብዙ ችግሮች ልክ ወያኔ እንደተወገደ ወዲያውኑ ይወገዳሉ ከሚሉት ተላላዎች ጋር የሚደመሩ ካሉ ይቀጥሉበት። ይሂዱበት። ምናልባትም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ ከነመለስ ጋር ሆነን የኢትዮጵያን ችግር እንቀርፋለን የሚለው ከንቱ ዕምነታቸው የሚሰምረላቸው ከሆነም ኅልም አይከለከልምና የዮሴፍን ችሎታ እንዲሰጣቸው እንመኝላቸዋለን። ኅልምን ማለማቸው የተፈጥሮ መብታቸው መሆኑን ብንረዳላቸውም፥ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያላሳተፈ ማንኛውም ብሔራዊ ጥረት ግን የትም እንደማይደርስ በዕርግጠኝነት መናገር የሚከብድ አይሆንም። ሁሉንም የፖሊቲካ ድርጅቶች፥ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፥ የሲቪክ ድርጅቶች፥ በጠቅላላውም የምልዐተ-ሕዝቡን ሁለንተናዊና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አግልሎ የት እንደሚደረስ፥ ሳይውል ሳያድር የሚታይ ጉዳይ በመሆኑ ፥ በዚህ ላይ መከራከሩ ጊዜ ማጥፋትና የወያኔን የፕሮፓጋንዳ መድረክ ማስፋፋት ይሆናል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ወያኔን አምርረው በመታገል ለሥርዓት ለውጥ ተግተው የሚሰሩ ድርጅቶች ዝግጁ አይደሉም።

ታሪክ በሌላ መልኳና ሁኔታ እራሷን ትደግማለች እንዲሉ፥ ዛሬም እንደ ትላንቱ፥ የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ኃይሎችንና ኅብረተስብ በልዩ ልዩ

የመከፋፋያ መስፈርት እየፈረጁ የተቃዋሚውን ጎራ ለመከፋፈል መፍጨርጨር ጊዜው ያለፈበት ትርኪ-ምርኪ ስለሆነ፥ ባይሰራም መሞከሩ አልቀረም። የሀገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች ቀኝና ግራ እያሉና በተለይም አንድን ጠንካራና አይበገሬነቱን ለወያኔ ባስመሰከረ ድርጅት ላይ በመረባረብ ወያኔን የመጥቅም ተልዕኳቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ። ይህም እንደማይሳካላቸ ከማንም በበለጠ ወያኔ እንደሚያፌዝባቸው የታወቀ ሆኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ላለፉት ሠላሳ ስድስት የመከራ ዓመታት የተማረው መራራ ተመክሮ ስለአለው ፥ በዚህ የመሰሪዎች ወጥመድ የሚገባ አይሆንም። በቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚሰማው አሳፋሪ ንግግር፤ እውነተኛውን ተቃዋሚ ኃይሎች ሁሉ፥ የብሄር ድርጅቶች፥ የግራና ቀኝ ፓርቲዎች፥ የኅብረ-ብሔር ድርጅቶች፥ አክራሪዎች ፥ ነፍጠኞች ወዘተ.. እያሉ የሚነዙት ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ነው። የዚህን ዓይነት ርካሽ የፕሮፓጋንዳ ጨዋታ እነ መለስ ዜናዊ ቢጫወቱ፥ ጭራሽ ሊያስገርም ባልቻለ ነበር። ወያኔን እንቃወማለን የሚሉት ክፍሎች ግን ይህንን ሲሉ የሚያስቅና የሚያስገርም ነው። አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት ይህንን በማድረጋቸው ለነ መለስ ዜናዊ የፖለቲካ ድልዳልና የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ጥይት ማቀበላቸውን መረዳት አለባቸው። ተወደደም ተጠላ፥ ይህ ዛሬ የሚካሄደው ትግል የብሔራዊ ነፃነት ትግል ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ በምንም ዓይነት የመከፋፋያ መስፈርትና አሰላለፍ ሳይራኮት፥ ሁሉም ተባብሮ ወያኔን ማስወገድና ሀገሩ ከገባችበት ውርደትና ከደረሰችበት የጥፋት ጠርዝ ማዳን፥ የቅድሚያ አጀንዳው እንደሆነ ተረድቷል። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የቆራጥ ተቃዋሚ ኃይሎችን አቋምና ትግል አጥብቆ የሚፈልገው፥ የሚደግፈውም። የሕዝብ ድጋፍ ሲባል፥ ለአንድ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ መውጣትን ብቻ ሳይሆን፥ ወይም በግብታዊነት በአንድ ስብሰባ የመጣውን የሕዝብ ቁጥር ብቻ ዓይቶ ለመርካት ሳይሆን፥ ያልተቋረጠ፥ ቀጣይነት ያለው ለጊዚያዊ የፖለቲካ ትኩሳት ራሱን ሰለባ ያላደረገ ሁለንተናዊ የሕዝብን ተሳትፎና ትብብርን ያቀነባበረ፥ የሕዝብ ትግል ሂደት ማለት ነው። በትግል ሂደት ውስጥ የሕዝብ ተሳትፎ ማለት ደግሞ፥ ከድሉም በኋላ፥ የሕዝብ ውሳኔና ይሁንታ አብሮ ስለሚቀጥል፥የአምባገነን ሥርዓት እንዳይመጣ ለማገድ አንድ መከላከያ ሊሆን የሚችልበት ዕድሉ የሰፋ ይሆናል ማለት ነው። ታዲያ ዛሬ የተቃዋሚውን ኃይል በተለያየ መልክ እየፈረጁ ለመከፋፍል የሚጥሩት ክፍሎች፥ የሕዝቡን ተሳትፎ የሚቃወሙት፥ ከሚያስቡት ዓላማቸው ጋር ስለሚፃረርባቸው ነው። የሕዝብን ተሳትፎ፤ ሙሉ ድጋፍ፥ ፍርድና ውሳኔ የሚፈራ ድርጅት ደግሞ፥ አንድ ምዕራፍ ጉዞ እንደማይሄድ የታወቀ ነው። ይህን ሀቅ ከተቀበልን ያለን ምርጫ አንድ ብቻ ነው። ቆራጥ ተቃዋሚውን ኃ ይልና ጎራ ማጠናከር ወሳኝ መሆኑን ተረድቶ ለዚህ ግብ ታጥቆ መሥራት!!